# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 140 ጥር 12 2003 ገጽ 1


**ቤን ዓሊ የአሜሪካና የአውሮፓ መንግሥታት የቅርብ ወዳጅ የነበረ ሰው ነው። በዓለም ዓቀፍ መገናኛ ብዙሃንም "የነፃ ገበያ አራማጅ፤ የፀረ-ሽብርተኝነት ትግል አጋር፤ የምዕራቡ ዓለምና የስልጣኔ ወዳጅ" እየተባለ ሲሞካሽ ነበር። በህዝብ ቁጣ ተፈንግሎ አገር ጥሎ ሲፈረጥጥ ግን ተሸናፊውን ቢን ዓሊን በማውገዝ አሜሪካንን የቀደመ የለም። አሜሪካ "ምንጊዜም ከቱኒዝያ ህዝብ ጎን እንደምትቆም" በመጀመሪያ ሂላሪ ክሊንተን ቀጥሎ ባራክ ኦባማ አረጋገጡ።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የአዲስ አበባ ወጣቶች የወያኔው አገዛዝ የከለከለውን ባንዲራ በጥምቀት በአል አውለበለቡ

በአዲስ አበባ የተከበረውን የጥምቀት በአል በደማቅ ሁኔታ ለማክበር በሚል ከአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች በቡድን የተደራጁ ወጣቶች በዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ልዩት ዕዛዝ ህዝብ በተሰበሰበባቸውና በማንኛውም አፊሴላዊ ቦታዎች እንዳይውለበለብ በአዋጂ ያገደውን በማሃሉ አንባሻ የሌለውን አረንጓደ ቢጫ ቀይ ቀለም የኢትዮጵያዊያን ስንደቅ አለማ በጉልበት በማውለብለብ ማሳለፋቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ሪፖርት ገልጹአል፣ ፤ ወጣቶቹ በዚሁ እለት በየአካባቢያቸው የሚገኙ የታቦት ማለፊያ መስመሮችን በራሳቸው ተነሳሽነት ማጽዳታቸውንና ቄጠማም መነዝነዛቸውን አክሎ ገልጹአል።

በወያኔ ድርጅታዊ መዋቅር የተደራጁ የከተማይቱ ልዩ ልዩ የወረዳ ባለሥልጣኖች በራሳቸው አነሳሽነት የተሰባሰቡትንና የታቦቱን መሄጃ መንገዶች በማጽዳት ላይ የነበሩትን እነዚህን ወጣቶች ለማስቆም ሞክረው እንደነበረና በተለይ አገዛዙ በአገሪቱ የትኛውም ክፍል አገልግሎት ላይ እንዳይውል የከለከለውን ባንዲራ እንዳያውለበልቡ ለማስፈራራት ያደረጉት ሙከራ አለመሳካቱን ዘጋቢያችን በቦታው ተገኝቶ እንደተመለከተ በላከው ሪፖርት ገልጹአል። በተፈጠረው ሁኔታ እጅግ የተደናገጡት የወያኔ ባለሥልጣናትና የደህንነት ሰዎች ከወጣቶቹ ጋር አታካሮ መግባት ወደ አልተጠበቀ አመጽ ሊሸጋገር ይችላል ከሚል ስጋት ዝም ብለው ከርቀት ሆነው ለመከታተል እንደተገደዱና እነርሱ "የጥፋት ኀይሎች" የሚሉዋቸው ተቃዋሚዎች መጠቀሚያ እንዳያደርጉዋቸው በማለት በከፍተኛ አይነ ቁራኛ ሲከታተሉዋቸው እንደዋሉ ለማወቅ ተችሎአል ። በቤተክሪስቲያኖች አካባቢ ያሉ የወያኔ ታማኝ አገልጋዮች ከጽጥታ ሃይሉች ጋር በመተባበር የወጣቶቹን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ ሲከታተሉ እንደነበር ፤ ተቃውሞ የሚያስነሳ ጽሁፍ ያለበት ቲ-ሸርት እንዳይለብሱ ፤ በ እጃቸውም ምንም አይነት ‹ተንኳሽ ጽሑፎች› ያለበት ነገር እንዳይይዙ ፤ ሲከታተሉ እንደነበር ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል። አንዳንድ ወጣቶች በጸጥታ ሃይሉ ሰራተኞች ቄጤማ ከመነዝነዝ እና ምንጣፍ ከማንጠፍ እንዲቆጠቡ፣ ወያኔ ያወጣውን የሰንደቅ ዓላማ አጠቃቀም መመሪያ እንዲያከብሩ ተነግሮአቸው እንደነበረ ነገር ግን ሰሚ እንዳላገኙ እንዲያውም አኛ የፈለግነውን ብናደርግ ምን ይመለከታችኋላ እስከማለት እንደደረሱ ታውቆአል።

ከዚህም ባለፈ መልኩ ለወያኔ ካደሩ የወጣቶችና ሴቶች ማህበራት በጥምቀት በአል የወያኔው አምባገነን አገዛዝ የከለከለውን ባንዲራ እናዳይጠቀሙ ማስፈራሪያና ዛቻ ለወጣቶች ቢያስተላልፉም ወጣቶቹ ይህን ዛቻ ከቁብ ሳይቆጥሩ በእምቢተኝነት የሚያምኑበትን የኢትዮጵያ ባንዲራ ማውለብለባቸውን ገልጾልናል።

ወጣቶቹ በራሳቸው ተነሳሽነት እንዴት እንዲህ አይነት ህብረት እንደፈጠሩና ለምንስ የወያኔን ባንዲራ አናውለበልብም እንዳሉ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው ወጣቶች እኛ በአምባገነኑ አገዛዝ ወኪሎች አማካኝነት ለሚቀርብ ጥሪ ሁሌም ቦታ አንሰጥም፣ እኛ የምንፈልገው በህዝብ የተመረጡ መሪዎች እንዲመሩን ነው፣ እስከዚያው ድረስ በራሳችን ተነሳሺነት የምናከናውናቸውን ተግባሮች ደስ ብሎን እናከናውናለን ብለዋል፣ ፤ ወጣቶቹ ቀጥለውም ወደፊትም ቢሆን ከወያኔው አገዛዝ የሚቀርብልንን ጥሪ በፈቃደኝነት አንቀበልም፣ ትክክለኛው ጊዜ ሲመጣና ሁኔታዎች ሲመቻቹልን ለዓለም ማንነታችንን እናሳያለን ሃገራችንንም ወደፊት እናራምዳለን በማለት መልሰዋል።

## የቱኒዚያው ማእበል የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት እያስጨነቀ መሆኑ ታወቀ

በቅርቡ ቱኒዚያ ውስጥ የተቀሰቀሰው የህዝብ አመጽ ተቀጣጥሎና ማእበልን ፈጥሮ የሃገሪቱ ፕሬዘዳንት ቢን አሊ ወደ ሳውዲ አረቢያ እንዲፈረጥጥ ማስገደዱ የታወቀ ሲሆን ይህን ክስተት ተከትሎ በወያኔው አምባገነን አገዛዝ ባለስልጣናት ላይ ጭንቀትና ውጥረት መፈጠሩን ዘጋቢያችን ታማኝ የሆኑ የውስጥ ምንጮችን በመጥቀስ ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ለማወቅ ችለናል።

በቱኒዚያ የታየውን ችግር የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በሚያስተዳድራቸው የአገር ውስጥ ዜና ማሰራጫ ጣቢያዎች አንድም ነገር እንዳይዘገብ እንዳስከለከለ፤ ህዝቡ ግን በሳታላይት አማካይነት ከውጪ ወደአገር በሚገቡት እንደ ኢሳት

ግዜ

ተሌቪዥን፤ ዶቼ ቨለ ፤ የአሜሪካ ን ድምጽ ሬዲዮ እና በግንቦት 7 ድምጽ ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተለ መሆኑን ከአገር ቤት እየደረሱን ያሉት መረጃዎች ይገልጻሉ።

በተያያዘ ዜና በሃገሪቱ የሚታተመውና ለመንግስት ቅርበት ያለው ሪፖርተር ጋዜጣ የወያኔው አገዛዝ በፖሊሲ ደረጃ ያስቀመጠው የዋጋ ዕድገት ከሰባት በመቶ መብለጥ ስለሌለበት በአንድ ጤናማ ኢኮኖሚ የዋጋ ዕድገት ከሰባት በመቶ በላይ ካለፈ አደጋ አለው በማለት የንግድ ሚኒስትር ዴኤታ አህመድ ቱሳን ጠቅሶ መዘገቡን ለማወቅ ተችሎአል። ።አህመድ ቱሳ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ በቱኒዝያ የፈጠረውን ችግር በማስታወስ ችግሩ እዚህ መደገም የለበትም ፤ በመሆኑም በኢትዮጵያ የዋጋ ንረቶች ከተቀመጣላቸው የዕድገት ደረጃ በላይ እንዳይሄዱ ማድረግ ያስፈልጋል ማለቱም ታውቁአል።

በሌላም በኩል የወያኔው አገዛዝ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ምክትል ዳይሬክተር ገብረ ዋህድ ወልደ ጊዮርጊስ በበኩሉ፣ የኑሮ ውድነቱ ጉልበተኛና ቀማኛ በመፍጠር አገር ችግር ውስጥ እንድትገባ ምክንያት ሊሆንና ሰላማዊ ኑሮንም ሊያደፈርስ ይችላል ማለቱንም ዘግቡአል።

ዘጋቢያችን ከዚሁ ጋር በማያያዝ በላከልን ዘገባ የወያኔው አምባገነን አገዛዝ በቅርቡ ዋጋን ለማረጋጋት በሚል የወሰደውን ዕርምጃ ተከትሎ በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎችን እየተወያዩ እንደሆነ ታውቁአል።

ከእነዚህ የውይይት መድረኮች አንዱ አሠሪዎች ፌዴሬሽን እየተባለ በሚጠራው የወያኔ አገዛዝ ተቁአም የተዘጋጀው አንዱ ሲሆን፣ ነጋዴዎችም የወያኔው አገዛዝ ይህን ዕርምጃ ከመውሰዱ በፊት ሊያወያየን ይገባ ነበር ማለታቸው ታውቁአል። ለሆዳቸው ያደሩና ዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ ወክለው የመጡት የሥራ ኃላፊዎችም በአገሪቱ ውስጥ የታየው ያልተገባ የዋጋ ግሽበት ትልቅ አደጋ ሆኗል፣ ግሽበቱ ደሃው ከሚሸከመው በላይ እየሆነ በመምጣቱ ለአገርም አደጋ ስለሆነ የዋጋ ቁጥጥሩን ማድረግ አስፈልጓል ብለዋል።

የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ባሁኑ ወቅት በወያኔው አገዛዝ ባለስልጣናት በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ የሆነ መደናገጥና ጭንቀት እየታየባቸው መሆኑን ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ ኢትዮጵያዊያን በቱኒዚያ በተፈጠረው ክስተት መደሰታቸውንና ከዚህም ተሞክሮ መውሰድ የሚገባቸውን ልምድ በማሰላሰል ላይ መሆናቸውን ገልጹአል።

## የዘረኛው አምባገነኑ ወያኔ አገዛዝ ማናለብኝነትና ጀብደኝነት ከልክ ማለፉ ተገለጸ

ባሳለፍነው ሳምንት በሃገር ውስጥ እየታተመ ለንባብ የሚወጣው "ፍትሕ" ጋዜጣ ባወጣው ዘገባ ራስ ዳሽን ተራራ በአዲሱ የተማሪዎች መማርያ መጻሕፍት ትግራይ ክልል ውስጥ እንደሚገኝ ተደርጎ መጻፉን መግለጹን ተከትሎ በርካታ የጎንደር ከተማ ነዋሪዎች ቁጪታቸውን እየገለጹ ነው።

ፍትህ ጋዜጣ አቶ ያሬድ የተባሉ የመኢአድ አባልን ዋቢ በማድረግ ጎንደር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ‹‹የትምክህተኞች መሠረተ ናት›› በሚል ምንም አይነት ልማት ሳይካሄድባት በተጽእኖ ስር እንደነበረች ገልጾ በጎንደር የነበሩት እነ ዴፖ፣ መብራት ኀይል፣ የትራክተር መገጣጠሚያዎች እና የዉሃ ማጣርያዎች "ተመዝብረው ወደ ትግራይ ተወስደዋል" ማለቱ ይታወቃል።

የራስ ዳሸን ተራራን ወደ ትግራይ ክልል የመካተቱን ጽሁፍ አስመልክቶ ዘጋቢያችን አስተያየት የጠየቃአቸው በርካታ የጎንደር ከተማ ነዋሪዎች እንደገለጹት፣ ይህ ጽሁፍ ቀልድ መሆን አለበት፣ ለዘመናት በጎንደር ክልል ውስጥ መሆኑ የሚታወቀውንና እጂግ በርካታ ለሆኑ ቱሪስቶች መስህብ እንደሆነ የሚታወቅን ክልል ወደትግራይ መውሰድ ማለት እውነትም የወያኔው አገዛዝ ከሚገባው በላይ ንቆናል ማለት ነው፣ ፤ ለማንኛውም ሂደቱን በንቃት እንከታተላለን ማለታቸውን ገልጾልናል።

ቀደም ብሎ "ከጎንደር ተቆርሶ ለሱዳን ይሰጥ የተባለውን መሬት የቀድሞው የአማራ ክልል ምክትል ፕሬዘዳንትና የአሁኑ ዋና ፕሬዘዳንት ደመቀ መኮነን በፊርማው ማጽደቁ ነገር ግን የቀድሞው የክልሉ ፕሬዝዳንት አቶ አያሌው ጎበዜ እና የጎንደር አስተዳዳሪ ጌታቸው ጀንበር አንፈርምም ብለው መቃወማቸው ይታወቃል።

ይህን የወያኔ አምባገነን አገዛዝ መሰሪ አካሄድ የተገነዘቡ አንድ የጎንደር ነዋሪ እንደገለጹት ቀደም ብሎ ከጎንደር እስከ ጋምቤላ የሚደርሰውን ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት በመስማማት ለሆዱ ያደረው ደመቀ መኮንን በፊርማው በማጽደቁ ለአከናወነው ተግባር የትምህርት ሚንስትር ሆኖ ተሾሞ እንደነበርና አሁንም አምባገነኑ አገዛዝ በአማራው ህዝብ ላይ የተለያዩ በደሎአችን ለመፈጸም እንዲመቸው ደመቀ መኮነንን የክልሉ ፕሬዘዳንት በማድረጉ ይህ የራስ ዳሸንን ወደ ትግራይ ክልል የመውሰዱ ስራ ተግባራዊ የማይሆንበት ምክንያት እንደማይኖር ግምታቸውን ገልጸዋል።

# ከቱኒዝያ ህዝባዊ ትግል የምንማራቸው ቁም ነገሮች

ዚን አል-አብዲን ቤን ዓሊ ለሃያ ሶስት ዓመታት ቱኒዚያና ህዝቧን ገዝቷል። ሞልቃቃዋ ሚስቱ ለይላ፣ ነሰሪንና ሌሎች አምስት ልጆቹ የቱኒዝያን ህዝብ ሃብት በመርጨት ተዝናንተዋል። የአገሪቱ መገናኛ ብዙሃን "ቱኒዝያ ቤን ዓሊን የመሰለ ምርጥ ልጅ ኖሯት አያውቅም" ሲሉ ቀስቅሰዋል። ቤን ዓሊ የአሜሪካና የአውሮፓ መንግሥታት የቅርብ ወዳጅ የነበረ ሰው ነው። በዓለም ዓቀፍ መገናኛ ብዙሃንም "የነፃ ገበያ አራማጅ፣ የፀረ-ሽብርተኝነት ትግል አጋር፣ የምዕራቡ ዓለምና የሰልጣኔ ወዳጅ" እየተባለ ተሞካሽቷል።

የቤን ዓሊ መንግሥትና ደጋፊዎቹ ስለ እድገትና ብልጽግና ቢያወሩም የህዝቡ የእለት ተእለት ኑሮ ግን እያሽቆለቆለ ነበር። ወጣቶች የዩኒቨርስቲ ትምህርት አጠናቀው ሥራ ማግኘት አልቻሉም። በአንፃሩ ደግሞ የቤን ዓሊን ቤተሰቦችና ደጋፊዎች ሁሉ በእጃቸው፣ ሁሉ በደጃቸው ነበር። ዝምድናና ወገንተኛነት የሁሉም ነገር ቁልፍ ሆነ። የቤን ዓሊን መንግሥት ሞልቶ ስለተትረፈረፈው ነፃነት ሲያወራ ህዝቡ ግን የልቡን ለመናገር ተከልክሎ እያጉረመረመ ነበር። ፖሊሱና ጆሮ ጠቢው የአገሬውን ሰው አገር አሳጣው። የቤን ዓሊ መንግሥት ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በማዳከሙ ህዝባዊው ትግል መሪ ያጣ መስሎ ነበር። ሆኖምቅራኔዎች በስለው ሰበብ ብቻ ነበር የሚፈልጉት።

ሰበቡ ባልታሰበ መንገድ ተገኘ። ባለፈው ወር ቅራኔው ፈነዳ። በዚህ ሳምንት ቱኒዝያ መስቀለኛ መንገድ ላይ ነች። ሁኔታዎች ወደየት እያመሩ እንደሆነ በግልጽ መናገር ባይቻልም የእያንዳንዱ እለት ውሎ የሃገሪቱን መፃዒ እድል የሚወስን እየመሰለ ነው። ታሪክ ሰሪዎቹ ከቤተመንግሥትም ሆነ ከሜካ ሳይሆን ከየጎዳናው እየወጡ ነው።

መሃመድ ቦዛዚ የሃያ አራት ዓመት የዩኒቨርስቲ ምሩቅ ቢሆንም ቋሚ ሥራ ግን አልነበረውም። ከቱኒዝ 150 ኪሜ ርቃ በምትገኝ ሲዲ ባውዚድ በምትባል ከተማ አትክልትና ፍራፍሬ እየሸጠ ይተዳደር ነበር። የከተማው ፖሊሶች "ንግድ ፈቃድ የለህም" በሚል በተደጋጋሚ እቃውን ዘረፉት፣ ሰደቡት፣ ደበደቡት። ወጣቱ መሃመድ ቦዛዚ እከተማው ማዘጋጃ ቤት በራፍ በገዛ ራሱ ላይ እሳት ለኮሰ፤ ከሁለት ቀናት በኋላም ህይወቱ አረፈች። ዜናው በፍጥነት ተሰራጨ። ይህ ከሆነ ከሁለት ቀናት በኋላ የሃያ ስድስት ዓመቱ ሁሴን ናጂ ፈልሂ "በቃኝ !!!! መረረኝ!!!" እያለ 30 000 ሜጋ ዋት የሚያስተላልፍ የኤሌክትሪክ ሽቦ ጨብጦ ሞተ። ሁሴን የዩኒቨርስቲ ምሩቅ ቢሆንም የቤን ዓሊ ዘመድ ባለመሆኑ ሥራ አጥ ነበር።

የሁለቱ ወጣቶች ምሬት የወለደው እርምጃ መላዋን ቱኒዝያ ናጣት። ተማሪዎች በቁጣ ወደጎዳና ወጡ፤ ሠራተኞች ተከተሏቸው። አስተማሪዎች፣ ሃኪሞች፣ ነርሶች፣ ነጋዴዎች፣ የቤት እመቤቶች የሥራ ልብሶቻቸውን እንደለበሱ ተማሪዎችን ተቀላቀሉ። ሁሉም ሰው፣ በሁሉም ቦታ፣ በአንድነት "መረረን!!! በቃን!!!" አለ። ቤን ዓሊ ዓልሞ ተኳሽ ወታደሮቹን አሰማራ፤ እነሱም ታንክ እየነዱ ከተማ ውስጥ ገቡ። እስካሁኗ ሰዓትም ከ100 በላይ ሰዎችን ገደሉ። ሆኖም ግን ታንኩ፣ ጥይቱ፣ የፖሊሶቹ አስለቃሽ ጋዝ የህዝቡን ቁጣ ማብረድ አልቻለም። የህዝቡ ጠንክሮ መቆም ወታደሮቹም በጭንቅላቶቻቸው እንዲያስቡ አደረጋቸው፤ እናም ቢን ዓሊ በተመኘው መጠን በህዝባቸው ላይ አልጨከኑም።

ቢን ዓሊ ድሮ ኢዲ አሚን ወደ ሸሸባት ሳዉዲ ዓረቢያ ፈረጠጠ። በአሁኑ ሰዓት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንዳንድ ተቃዋሚዎች የተሳተፉበት ጊዜዓዊ መንግሥት አቋቁሞ በስድስት ወራት ውስጥ አዲስ መንግሥት መመስረት እንዲቻል ህዝቡ እንዲረጋጋለት በመለማመጥ ላይ ነው። ተገፍተው አገር ለቀው የነበሩ የፖለቲካ መሪዎችም እየተመለሱ ነው። አሁን መንግሥት ለማኝ፤ ህዝብ ተለማኝ ሆኗል። ቱኒዚያ ግን ገና አልተረጋጋችም።

ተሸናፊውን ቢን ዓሊን በማውገዝ አሜሪካንን የቀደመ የለም። አሜሪካ "ምንጊዜም ከቱኒዝያ ህዝብ ጎን እንደምትቆም" በመጀመሪያ ሂላሪ ክሊንተን ቀጥሎ ባራክ ኦባማ አረጋገጡ። ቀጥላ የቀድሞ ቅኝ ገዥዋ ፈረንሳይ የቱኒዚያ ህዝብ "አጋርነትዋን" በተግባር ለማረጋገጥ ለአንድ ለሊት ለመኝታ ብቻ አምስት መቶ ኢ.ውሮ በሚከፈልበት ልዩ ሆቴል በመዝናናት ላይ የነበረችው የቢን ዓሊ ልጅ - ነሰሪን - ፈረንሳይን ለቃ እንድትወጣ አደርጋለሁ ስትል ዛተች። ቤን ዓሊ ወደ ፈረንሳይ ለመሸሽ ቢያስብም የመግቢያ ፈቃድ ከለከለችው። የቱኒዝያ ጉዳይ በእንግሊዝ ፓርላማም ተነስቶ ሥልጣን ላይ ያሉትም የሌሉትም የፓርላማ አባላት በአንድ ድምጽ ቤን ዓሊን በማውገዝ "ከቱኒዝያ ህዝብ ጎን" ቆሙ።

ዓለም ዓቀፍ ሚዲያዎች በቱኒዚያ እየሆነ ያለውን ነገር ለመዘገብ ብቻ ሳይሆን፤ የቢን ዓሊንና የሚስቱን የለይላን ጥፋቶች ለመዘርዘር ሰዓታት የፈጁ ፕሮግራሞችን ሰርተው ዓየር ላይ ለቀቁ። ሚዲያዎቹ ለይላን ሶስት ሺህ ጥንድ ጫማዎች ከነበሯት ከፊሊፒንሷ ሞልቃቃ ኤሜልዳ ማርቆስ ጋር እያነፃፀሩ በስግብግቧ ተሳለቁባት።

የቱኒዝያ ህዝብ ትግል ቀጥሏል። ይህ ትግል ወደየት እንደሚያመራ መገመት ለጊዜው ከባድ ነው።

ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እስካሁን ባየነው እንኳን ቢሆን ከቱኒዚያው ህዝባዊ ትግል የምንማራቸው በርካታ ቁምነገሮች አሉ ብሎ ያምናል፤ ለጊዜው ግን በሚከተሉት ሶስት ዓብይት ነገሮች ላይ እናተኩራለን።

1. አምባገነን ሥርዓቶች አስከፊ ውድቀት ይወድቃሉ። አምባገነኖች ከታሪክ መማር የማይችሉ በመሆናቸው ውድቀታቸውን ማሳመር አይችሉም። ወታደርና ሃብት ከውድቀት አያድኑም።
2. ህዝብ ከፍርሃት ቆፈን ከተላቀቀ መሳሪያ አይገታውም። ከፍርሃት የተላቀቀ ህዝብ ራሱን ለማደራጀትና መሪዎችን ለመምረጥ ጊዜ አይወስድበትም። ቀደም ባሉ ዓመታት በዩክሬንና በጆርጂያ የታዩ ህዝባዊ የጎዳና ላይ አመፆች በአፍሪካ ምድርም የሚቻሉ መሆኑን ቱኒዚያዊያን በተግባር አስመስክረዋል።
3. የኃያላን መንግሥታትን ድጋፍ ለማግኘት የህዝባዊ ንቅናቄው በዓላማና በሞራል ከአምባገነኖቹ በልጦ መገኘት በቂ አይደለም። የኃያላኑን ድጋፍ ለማግኘት አንባገነኑን ማንበርከክ የሚችል ኃይል ሆኖ ጠንክሮ መታየት ግድ ነው።

ቢን ዓሊ ቱኒዝያ ውስጥ የገነባው ሥርዓት መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተከለው አገዛዝ በብዙ እጥፍ የተሻለ ነበር። መለስ የቢን ዓሊን ጥፋቶችን በብዙ እጥፍ ከመስራቱ በተጨማሪ በሌላ ማንኛውም አገር የሌለ ትልቅ ክፋት እኛ ላይ እየፈፀመብን ነው። ይህ የክፋቶች ሁሉ ቁንጮ - መዋቅራዊ ዘረኝነት ነው። መለስ ዜናዊ ዘረኝነት የአገዛዙ መሠረት አድርጎታል። እናም ቱኒስ የተነሳው ነፋስ አዲስ አበባ ሲደርስ እንደምን ያለ አውሎ ነፋስ እንደሚወጣው መገመት ከባድ ነው። በእኛ ተጨባጭ ሁኔታ የተደራጀ አካል የመኖሩ አስፈላጊነት የጎላ የሚያደርገውም በእንዲህ ዓይነት ወቅት ዘረኝነት ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ተከላክሎ ንቅናቄው ግቡን እንዲመታ ማድረግ ስለሚገባ ነው። ሁላችንም ለዚህ ዝግጁ እንሁን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

## የወያኔ አገዛዝ በኑሮ ውድነት ምክንያት ህዝብ ይነሳብኛል የሚል ስጋት አለበት ተባለ

የኑሮ ውድነት ብዙሃኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ለረሃብ እና ለችጋር እየዳረገ ባለበት፣ የዋጋ ንረት እየጨመረ እንደሄደ ዘገባዎች አመልክተዋል። የታህሳስ ወር የምግብና የሌሎች ሸቀጣሸቀጦች ዋጋ ከህዳር ወር ጋር ሲነጻጸር ከአራት በመቶ በላይ ጭማሪ ማድረጉን ሬውተርስ የዜና አገልግሎት በአገዛዙ ቁጥጥር ስር ያለውን የእስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ጠቅሶ ዘግቧል። ይህ የአራት በመቶ ጭማሪ ደግሞ ቀድሞውኑ ከናረ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በመሆኑ፤ የሸቀጣሸቀጦች ዋጋ ከጥቂት አመታት በፊት ከነበረበት ጋር ሲነጻጸር በብዙ እጥፍ ማሻቀቡን ያሳያል። የዜና አውታሩ እንደ ዳቦ ያሉ ምግቦች ዋጋ ባለፈው አመት ብቻ ዋጋቸው በእጥፍ መጨመሩን አመልክቷል።

አገዛዙ የዋጋ ንረት በሚቀጥሉት አምስት አመታት ይቀንሳል ብሎ ቃል ቢገባም፤ ከአሁኑ መቆጣጠር ተስኖት እራሱ ለፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ ነጋዴዎችን ማጥቃት ጀምሯል። የኢኮኖሚ ተንታኞች የዋጋ ንረቱ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ እንደማይሄድ እንደሚተነብዩ የሬውተርስ ዘገባ ጠቅሷል።

ከሁለት አመታት በፊት እንደ ግብጽ እና ሃይቲ ባሉ አገራት በተከሰተው የምግብ ዋጋ ንረት ምክንያት ህዝባዊ አመጽ መፈንዳቱ ይታወሳል። በወቅቱ በነዚህ አገራት የነበረው ንረት አሁን ኢትዮጵያ ካለው ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው። መለስ ዜናዊ እና የቅርብ አማካሪዎቹ ከዚህ የተነሳ ከፍተኛ ጥበት ላይ እንደሚገኙ አንዳንድ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ።

የዝግጅት ክፍላችን ያናገራቸው የፖለቲካ ተንታኝም፥ በቅርብ ጊዜ በነጋዴዎች ላይ የተከፈተው ጥቃት አገዛዙ ያለበትን የስጋት ደረጃ የሚያንጸባርቅ ነው ይላሉ። በርግጥም ነጋዴዎችን ከገበያ አስወጥቶ ኢኮኖሚውን ከአንድ ዘር በተውጣጡ ምርጦች ቁጥጥር ስር ማዋል ከመሰረታዊ አላማው ጋር የሚሄድ ቢሆንም፤ መለስ ዜናዊ ህዝቡ የኑሮ ውድነቱ ከሚሸከመው በላይ እንደሆነበት ሳይገነዘብ አይቀርም ብለዋል።

በቅርቡ በወንጂ ስኳር ፋብሪካ የተከሰተው የስራ ማቆም አድማ፤ የሱሉልታ ነዋሪዎች በአገዛዙ ባለስልጣናት ላይ የፈጸሙት ጥቃት፤ ቢጋምቢላ፣ በአላማጣ እና እንዲሁም በአፋር ህዝቡ በተናጠል እየወሰዳቸው ያሉት እርምጃዎች፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ተቃውሞ እና የመሳሰሉት፤ ላለፉት ጥቂት አመታት ታፍኖ የቆየው ህዝብ በምሬት እየተነሳሳ ስለመሆኑ አመላካች በመሆናቸው በአገዛዙ ላይ ከፍተኛ ስጋት ሳይፈጥር እንዳልቀረ የፖለቲካ ተንታኙ ግምታቸውን ገልጸዋል።

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መዋቅራዊ ዘረኛነትን በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥም እያስፋፋ እንደሆነ ተነገረ

የኢትዮጵያን የመንግስት ስልጣን ከአንድ ዘር በተውጣጡ ጥቂቶች ቁጥጥር ስር ያዋለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የዘር አድሎ ምህዳሩን ከጊዜ ወደጊዜ እያሰፋ ሄዶ በአሁኑ ሰዓት መዋቅራዊ ዘረኛነትን በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ እያሰፈነ እንደሆነ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ለሪፖርተራችን ገልጸዋል።

አየር መንገዱን ወደ ከፍተኛ የስኬት ደረጃ እንዳወጡ የሚነገርላቸው የቀድሞ ስራ አስኪያጅ ግርማ ዋቄ በሰኔ 2001 በፓርላማ ኮሚቴ ፊት ቀርበው ባደረጉት ንግግር ድርጅቱ በዘር ላይ የተመሰረተ የሰራተኛ ቅጥር እንዲፈጸም በአገዛዙ ጫና እየተደረገበት እንደሆነና በዚህም ምክንያት አደጋ እንዳንዣበበበት ማስጠንቀቃቸው ይታወሳል። ግርማ ዋቄ ባለፈው መስከረም ከስራቸው ተወግደው የትግራዩ ገዢ ቡድን አባል ተወልደ ገብረማሪያምም መሾሙ ይታወቃል።

(ወደ ገጽ 5 ዞሯል)

# የቱኒዚያዊያኑ የበቃኝ ርምጃና ተሞክሮው

በቃኝ! በቃኝ! በቃኝ! መረገጥ በቃኝ! መዘረፍ በቃኝ! መገደል በቃኝ! መታሰር በቃኝ! መዋረድ በቃኝ! ። ህዝቡን እንደ ጠላት ረግጦ ሲገዛ የቆየውን አምባገነን፣ ከስልጣን ያባረረው የቱኒዚያ ህዝብ ድምጽ!

ለሃያ ሶስት አመታት በብረት በትር ከገዛ በኋላ በህዝባዊ አመጽ ከስልጣኑ የተፈነገለው እና ባለፈው አርብ ከአገሩ ሸሽቶ የወጣው የቱኒዚያው ዚን ኤል አቢዲን ቤን አሊ በሚያስገርም ሁኔታ ኢትዮጵያን በጉልበት ከሚገዛው መለስ ዜናዊ ጋር ተመሳሳይ ታሪክ አለው።

ቤን አሊ ከሱ ቀድሞ የነበረውን ገዢ በብቃት ጉድለት እና በጭካኔ ወቅሶ፤ ዴሞክራሲ እና ለውጥን ቃል ገብቶ ወደ ስልጣን የመጣው እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1987 ነበር። ወደ ስልጣን ከመውጣቱ በፊት በአገሪቱ የደህንነት ተቋማት ውስጥ ለበርካታ አመታት የሰራው ግለሰብ ግን፣ በቱኒዚያ ዴሞክራሲን የማስፈን አላማ እንደሌለው ለማሳየት አንድ የምርጫ ዘመን አልፈጀበትም።

ቤን አሊ በቱኒዚያ የውትድርና እና የደህንነት መዋቅራት ውስጥ በነበረባቸው ጊዜያት በገነባው ድጋፍ ላይ ተንተርሶ በህዝቡ ውስጥ ፍርሃትን በማስፈን የሚገዛን አምባገነናዊ ስርአት ገነባ። ስልጣን በያዘ በስድስተኛ አመቱ ባካሄደው ምርጫ ተብዬ መቶ በመቶ አሸፍኩ አለ። ከአምስት አመታት በኋላ በተካሄደው ምርጫ 99.4 በመቶ፤ ባለፈው አመት በተካሄደው ደግሞ 90 በመቶ።

እንደሱ ካሉ አምባገነናዊ አገዛዞች በሚጠበቅ መልኩም፥ የሰብአዊ መብት ረገጣ በቱኒዚያ ውስጥ ሰፈነ። ህዝቡ እራሱን የመግለጽ እና የመሰባሰብ መብቱን ተነጠቀ፤ ጋዜጠኞች ታፈኑ፣ ተሰደዱ፤ በርካታ ዜጎች ተገደሉ፣ ታሰሩ፣ ለሰቆቃ ተዳረጉ። በአገሪቱ ውስጥ እና በውጪ ያሉ የገለልተኛ መረጃ አውታሮች ታፈኑ፤ ዜጎች በጨለማ እንዲኖሩ ተፈረደባቸው። እንዲህ አይነቱ ግፍ ለኛ አዲስ አይደለም።

የቤን አሊ አገዛዝ ከሰብአዊ መብት ረገጣና አፈና ባሻገር፤ እንደ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ሁሉ፥ በሙስና፣ በአድሎ፣ በስራ አጥነት እና በኑሮ ውድነት ቀለሞች ያጌጠ ነበር። በተለይም፥ የቤን አሊ ቤተሰቦች እና የነገዱ አባላት፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ በስራ አጥነት በሚሰቃይበት አገር፣ አብዛኛውን ትርፋማ የንግድ ዘርፍ ሁሉ ተቆጣጥረው ሃብት አጋበሱ። ከመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን ሁኔታ ጋር እጅጉን በሚመሳሰል መልኩ፤ የአምባገነኑ ባለቤት ለኢላ ትራበልሲ ከህዝብ በተሰረቀ ሃብት አጌጠች፣ አሸበረቀች፤ በውጭ አገራት የከፈተቻቸው የባንክ ሂሳቦች ሞልተው አፈሰሱ።

ልክ እንደ አዜብ መስፍን፥ ለኢላ ትራበልሲም ዘራፊነቷን ለመደበቅ እና የህዝብ ሰው ለመምሰል የከፈተቻቸው እና የመራቻቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እውነተኛ ማንነቷን ሊደብቁላት አልቻሉም።

የመንግስትን የደህንነት እና የመከላከያ መዋቅር በመጠቀም አንገቱን በረገጡት ህዝብ ላይ የተሳለቁት እነዚህ ባል እና ሚስት፣ የቱኒዚያዎቹ ቻውሴስኮዎች ተብለው ተጠርተዋል። ኒኮላ እና ኢሌና ቻውሴስኮ ሮማንያን ለሃያ ሁለት አመታት ረግጠው የገዙ እና የዘረፉ ባልና ሚስት መሆናቸው ይታወሳል። ከሃያ አንድ አመታት በፊት አገዛዛቸው በህዝባዊ አመጽ ከተገለበጠ በኋላም፤ ሁለቱም ተረሽነው አስከሬናቸው በቴሌቪዥን ታይቷል።

የኢሌና ቻውሴስኮን እና የአዜብ መስፍንን ተመሳሳይነት ከዚህ ቀደም ዘርዝረን ነበር። ሁለቱም በባለቤቶቻቸው ላይ ተንጠላጥለው ስልጣን በስልጣን ላይ የደራረቡ፤ ከህዝብ የዘረፉትን ገንዘብ ወደ ውጭ ያሸሹ፤ ህዝብ ሲራብ በውድ ልብስና ጌጥ ያሸበረቁ፤ ሰነፍ ተማሪዎች ሆነው ሳለ የውሸት ዲግሪዎች ያሰባሰቡ፤ እውነተኛ ማንነታቸውን ለመደበቅ በጎ አድራጊ መስለው ለመታየት የሚጥሩ፤ እንዲሁም ጉቦ በመስጠት ሽልማት እና ሙገሳን ከተለያዩ ተቋማት የሚያሰባስቡ መሆናቸውን አሳይተናል።

ታዲያ፥ ቤን አሊ እና ሚስቱ እንደ ቻውሴስኮዎች እንደ ረገጡት እና እንደዘረፉት የተረዳው የቱኒዚያ ህዝብ...መጨረሻቸውንም እንደነሱው ለማድረግ ቆርጦ ሳይነሳ አልቀረም።

የቤን አሊን እና የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ከሚያመሳስላቸው ነጥቦች ውስጥ ሌላው፣ ሁለቱም ከውጭ አገራት፣ በተለይም ከምእራባውያኑ ጋር፣ ያላቸው ግንኙነት ነው።

ቤን አሊ በተለይ ከዛሬ ዘጠኝ አመታት በፊት በአሜሪካ ላይ የደረሰውን የሽብርተኞች ጥቃት ተከትሎ እንደ ብዙ የአለማችን አምባገነኖች እራሱን "ጸረ-ሽብርተኛ" ብሎ በመሾምና ከአሜሪካኖቹ ጋር በመወገን ድጋፋቸውን ለማግኘት ችሏል። እነሱም በህዝቡ ላይ ለሚፈጽመው ግፍ ጀርባቸውን ሰጡ። እንደ ፈረንሳይ ያሉ አገራትም እንዲሁ።

ባለፈው አመት በቱኒዚያ በተደረገው ምርጫ፣ ቤን አሊ 90 በመቶ በሚሆነው ድምጽ አሸንፌያለሁ ብሎ ሲያውጅ፤ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ አገዛዙ ለአለም አቀፍ ታዛቢዎች በሩን አለመክፈቱን አውግዞ፣ ከቱኒዚያ ፕሬዚደንት እና መንግስት ጋር ያለውን ግንኙነት ግን አጠንክሮ እንደሚቀጥልበት ገልጿል። የወያኔ አገዛዝ ባለፈው አመት ካካሄደው የምርጫ ተውኔት በኋላ ምእራባውያኑ እንዲሁ ማለታቸውን ልብ ይሏል።

ከሁሉ ባሻገር ደግሞ፥ ምእራባውያኑ በቱኒዚያ ይሰሙ የነበሩትን የለውጥ ድምጾች ይመቱ የነበረበት ክርክር ስለኛም ከሚናገሩት ጋር ተመሳሳይ ነው። "በቱኒዚያ የኢኮኖሚ እድገት እየታየ ነው፣ እሱን ካገኙ ዴሞክራሲ ምን ያረግላቸዋል።" "በቱኒዚያ ጠንካራ ተቃዋሚ ቡድን የለም፤ ቤን አሊ ቢወርድ ስልጣን ማን ይረከባል፤ ቢያንስ እሱ መረጋጋትን አስፍኗል።" እና የመሳሰሉት አስተያየቶች ይሰጡ ነበር። በዚህም ምክንያት፣ የቱኒዚያ ህዝብ ሲገደል፣ ሲታሰር፣ ሰቆቃ ሲደርስበት፣ በስራ አጥነት እና በኑሮ ውድነት ሲንገላታ ሃያላኑ አገራት ዝም አሉ።

የቱኒዚያ የቀድሞ ቅኝ ገዢ ፈረንሳይ ደግሞ የባሰውኑ በህዝባዊ አመጹ ምክንያት የተነሳውን አለመረጋጋት በቁጥጥር ስር ለማዋል ቤን አሊን እንደምትረዳ አመላከተች። አመጹ ተስፋፍቶ ቤን አሊ እስኪፈረጥጥ ድረስም ዝም አለች።

እንግዲህ አምባገነኖች የፈለጉትን ያህል ቢጠነከሩ፤ ህዝብ የሚረዳው ሃያል አገር ቢያጣ፤ አይሆንልህም፤ እራስህን በራስህ ማስተዳደር አትችልም፤ ልዩ መሪ ያስፈልግሃል፤ ያንን ደግሞ ስለሌለህ ላለህ አምባገነን አጎንብሰህ ለዘላለም ተገዛ ተብሎ ቢፈረድበትም፤ በቃኝ ብሎ የፈነዳ ለታ ሊያቆመው የሚችል ሃይል እንደሌለ የአለማችን ታሪክ አሳይቶናል። በቱኒዚያ የሆነውም ይኸው ነው።

ሙሃመድ አል ቦዚዚ የሃያ ስድስት አመት ቱኒዚያዊ ወጣት ነበር። የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ ቢኖረውም፤ በቤን አሊ የተዛባ የኢኮኖሚ ፖሊሲና አገሪቱ ከተዘፈቀችበት ሙስና እና ዘረፋ የተነሳ እንደ ብዙ ቱኒዚያውያን ወጣቶች ስራ አልነበረውም።

ታዲያ፥ ታታሪዎቹ የኢትዮጵያ ወጣቶች እንደሚያደርጉት ሁሉ፣ እራሱን እና ቤተሰቡን ለመርዳት ቆርጦ የተነሳው ወጣት፣ ሲዲ ቦዚድ በተባለችው ከተማው ጎዳናዎች ዳርቻ ላይ ፍራፍሬ እና አትክልት በመሸጥ ድህነቱን መዋጋቱን ተያያዘው። ይሄ ግን፥ ቀድሞውን የልጁን እጣ ፈንታ ለሰረቁት፣ ኑሮውን የድህነት መቀመቅ ውስጥ ለከተቱት የአምባገነናዊው አገዛዝ ቅጥረኞች ተቀባይነት አልነበረውም። የንግድ ፍቃድ የለውም በሚል ሰበብ ፖሊሶች ምርቱን ቀሙት፤ መደቡንም አፈረሱበት።

ከአንድ ሳምንት በፊት በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ መገናኛ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሆነውም ይኸው ነው። እራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን ከረሃብ ለማዳን እመንገድ ላይ ሸቀጣሸቀጥ በመሸጥ ትርፍ ለማግኘት የሞከሩ ወጣቶች፣ የጠላት ወታደሮች እንደሚያደርጉት በዘረኛው አገዛዝ ፌዴራል ፖሊስ ተከበው እቃቸውን ተቀምተዋል፤ በእንባ እየተራጨም ተስፋ ወደጠፋባቸው የአዲስ አበባ ጎዳናዎች ተበታትነዋል።

ሙሃመድ አል ቦዚዚ ግን አልቅሶ ወይም ተናዶ ዝም አላለም። የሱ ቁጣ እና ተስፋ መቁረጥ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ነበር። የሃያ ስድስት አመቱ ወጣት ታህሳስ 9 ቀን 2003 አመተ ምህረት ከአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ፊት ለፊት ቆሞ በራሱ ላይ እሳት አቀጣጠለ።

የሙሃመድ አል ቦዚዚ እርምጃም፣ እንደ ክብሪት ሆና የቱኒዚያን ህዝብ ቁጣ ጫረች....

ወጣቱ እራሱን ካቃጠለ በኋላ የፈነዳው ህዝባዊ ተቃውሞ፣ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ እየዘለለ ምድሪቱን አጥለቀለቃት። የቤን አሊ መንግስት የአገሪቱን መከላከያ ሃላፊ ህዝቡን እንዲያጠቃ አዘዘ፤ ሃላፊው እምቢ አለ፤ ከስልጣኑም ተወገደ። በኢትዮጵያችን ቁልፍ የመከላከያ የስልጣን መቀመጫዎች በሙሉ በዘረኞች በመያዛቸው፤ እንደዚህ ግለሰብ ወቃሽ ህሊና ይኖራቸዋል ብሎ ለማሰብ ይከብዳል።

እናም አምባገነኑ ቤን አሊ ወታደሮቹን እና ፖሊሶቹን በህዝቡ ላይ አዘመተ። በአስርት የሚቆጠሩ ተገደሉ፤ መቶዎች ቆሰሉ፤ በርካቶች ታሰሩ። ጋዜጠኞች እና የኢንተርኔት ላይ ጸሃፊዎች ከያሉበት ተለቀሙ። ከ1997 ምርጫ በኋላ መለስ ዜናዊ በህዝብ ላይ ያካሄደው ጥቃት አይነት በቱኒዚያም ተከሰተ።

ህዝቡ ግን አልቆም አለ። "ቤን አሊ ውጣ ውጣ!" "ቤን አሊ ዘመንህ አልቋል!" እያለም ጮኸ። የደህንነት ሰራተኞቹ እና ወታደሮቹ የአፈና ሙከራቸውን አፋፋሙት። ሰልፈኞቹን በየቦታው በማገት እና በማጥቃት ለማስቆም ሞከሩ። ይሁን እንጂ፥ ወጣቶች በተለያዩ አካባቢዎች በራሳቸው በመሰባሰብ በተናጠል ሰልፍ ማድረግ ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ሁኔታው ከቁጥጥራቸው ውጪ የሆነው የአገዛዙ ቅጥረኞች፤ ሰዓት እላፊ ለመጣል ሞከሩ። ለጊዜውም ፋታ ያገኙ መሰለ... ይሁን እንጂ ያልተበገሩ ጥቂቶች ትእዛዝ እየጣሱ በመውጣት ህዝቡን ያነሳሱት ነበር።

ይህ፥ የአንድ ሰዓት እላፊ ትእዛዝ ሰባሪ ቱኒዚያዊ ድምጽ ነው...

*"ቱኒዚያ ለዘላለም ትኑር! የቱኒዚያ ህዝብ ዛሬ ነጻ ነው! የቱኒዚያ ህዝብ ሆይ ተነስ! አትፍራ! የቱኒዚያ ህዝብ አይፈራም! አምባገነኑ ሸሽቷል! ዛሬ ነጻ ህዝብ ነን! የቱኒዚያ ህዝብ አይፈራም! የቱኒዚያ ህዝብ ሆይ እራስህን ከፍ ከፍ አድርግ! እንስሳው ቤን አሊ ፈርጥጧል! በዚህ ምሽት ነጻ ወጥተሃል! ነፃነት ለዘላለም ትኑር!"*

አዎን፥ ያልተበገሩት ጥቂቶች...ነገሮች ጋብ ያሉ ሲመስሉ፤ ዝም ያሉ ሲመስሉ፤ ክፍተቱን በድፍረታቸው ይሞላሉ!

የቱኒዚያው ህዝባዊ አመጽ ዋና ከተማው ደረሰ። በአስር ሺሆች የሚቆጠሩ ጎዳናዎቹን አጥለቀለቁ። ቤን አሊ ከስልጣን እንዲወገድ ጥሪ ቀረበ።

ገድሎ፣ ደብድቦ እና አስሮ አልሆንለት ያለው አምባገነን፤ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የቱኒዚያዊያኑ የበቃኝ ርምጃና . . . (ከገጽ 3 የዞረ)

አሁን በተስፋ መቁረጥ ብዙም ያላሰበባቸውን እርምጃዎች መውሰድ ጀምሯል። ህዝቡን ሲያስገድል የቆየው እሱ መሆኑን ለመሸፈን የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴሩን ወንጅሎ ከስልጣን አባሮታል። ህዝብ ግን አልታለለም።

ቤን አሊ በጥድፊያ ቃል መግባት ጀመረ። "ቃል እገባለሁ...በአጭር ጊዜ ውስጥ በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ ስራዎችን እፈጥራለሁ። የኑሮ ውድነቱን በቁጥጥር ስር አውላለሁ። ዴሞክራሲን አሰፍናለሁ። ከአራት አመታት በኋላ የስልጣን ዘመኔ ሲያልቅ እወርዳለሁ።" እና የመሳሰሉትን ተናገረ። ህዝብ አልሰማ አለ። ቀጥሎ ደግሞ "እሺ በስድስት ወራት ውስጥ አዲስ ምርጫ አካሄዳለሁ አለ።"

አምባገነኖች አጣብቂኝ ውስጥ ሲገቡ የማይናገሩት የለም፤ ይህን እኛም እናውቀዋለን። መለስ ዜናዊ ከአመት አመት የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም ሲል የማይገባው ቃል፣ የማይዋሸው ውሸት እንደሌለ እናውቃለን። ወደፊትም የበለጠ አጣብቂኝ ውስጥ ሲገባ፤ ከዚህም የባሰ ውሸት እንደሚዋሽ እና ቃል በቃል ላይ እንደሚያዥጎደጉድ ይጠበቃል። ሰሞኑን የኑሮ ውድነትን እቆጣጠራለሁ ብሎ መፎከሩም ከዚሁ የሚመደብ ነው። ታዲያ የቱኒዚያ ህዝብ በቤን አሊ የቃላት ውዥንብር አልተታለለም። ከአመት አመት የአምባገነኑን ውሸት መስማት በቅቶት ስለነበር!

በዚህ ወቅት ከአገሪቱ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች አንዱ እንዲህ የሚል ንግግር አደረጉ፦

*"ወንድሞቼ እና እህቶቼ፦ ቤን አሊ ውሸታም ነው። ልናምነው አንችልም። በሙስና ለተዘፈቀው አገዛዙ ተጨማሪ ጊዜን ለማግዛት እየሞከረ ነው። ከዚህ ቀደም ዴሞክራሲያን እንደሚያሰፈን ቃል ገብቶልን ነበር፤ የሰጠን ግን እስር ቤቶችን እና ሰቆቃን ነው። ባለፉት ሁለት ሳምንታት በቤን አሊ ትእዛዝ ከ90 በላይ ዜጎች ተገድለዋል። ይህ ሰው ሊወገድ ይገባዋል። ከስልጣን ሊወርድ ይገባዋል። ለፈጸመው ወንጀል እና ሙስና እንዲጠየቅም ፍርድ ፊት መቅረብ አለበት። ወንድሞቼ እና እህቶቼ፦ አሁን ልናቆም እና እጃችንን ልንሰጥ አንችልም! በዚህ ዘራፊ አገዛዝ ላይ ጫናችንን ልናጠናክር ይገባናል። ቤን አሊን ከስልጣን እስከናስወግድ እና ዴሞክራሲያዊ፣ እንዲሁም ህግ እና ሰብአዊ መብት አክባሪ የሆነን ስርአት እስክንገነባ ድረስ አንድ ሆነን መቀጠል አለብን። እንበርታ፤ ድላችን ቅርብ ናት!"*

ይህ ንግግር የህዝቡን ስሜት የገለጸ ሆነ። ቱኒዚያውያን የቤን አሊን "የላም አለኝ በሰማይ" ቃላት አልሰማ አሉ። "ቤን አሊ ውሸታም ነው"፤ "ቤን አሊ ዘመንህ አልቋል"፤ "ጫወታው አልቋል"፤ "ቤን አሊ ውጣ" የሚሉ መፈክሮች ተሰሙ።

ህዝቡ ሰልፉን በድፍረት ቀጠለ። በብዛቱም ፖሊሶቹን እና ወታደሮቹን ዋጣቸው። የወታደሮቹ አዛዦች ቤን አሊ ፈርጥጦ ሲሄድ ምን እንደሚውጣቸው በማሰብ በፍርሃት ተወጠሩ። በስተመጨረሻም፣ ፖሊሶቹም፣ ወታደሮቹም፣ ውሸቱም ሊያድነው እንደማይችል የተረዳው አምባገነን አገሩን ጥሎ አንበሳ እንዳየች ውሻ ጅራቱን በሁለት እግሮቹ መካከል ሸጉጦ ፈረጠጠ። በግል አውሮፕላኑ ላይ ወጥቶ ከአገር አገር ሲንከራተት ከቆየ በኋላ በስተመጨረሻ ሳውዲ አረቢያ ጥገኝነት ማግኘቱ ታወቀ። ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሰልፈኞቹ የአምባገነኑን ሚስት የለኢላ ትራብልሲን ቤተሰብ ንብረቶች መዝረፍ እንደጀመሩ ሪፖርቶች ተሰሙ። ቤተሰቦቿም አገር ጥለው ወደ ፈረንሳይ ሸሹ።

ቤን አሊ መውደቁን ያስተዋሉት የቀድሞ ምእራባውያን ጓዶቹ በአንድ ጊዜ ከዱት፤ ዞር ብለውም የቱኒዚያን ህዝብ እንደሚደግፉ አስታወቁ። ከበርካታ ወራት በፊት እንዲሁ በህዝባዊ አመጽ የተባረረው የኪርጊስታኑ አምባገነን መሸሹን ሲሰሙም ምእራባውያን እንዴት ፈጥነው እንደከዱት ይታወሳል። እስከ መጨረሻው ጸጥ ብላ የቆየችው ፈረንሳይ ቤን አሊን እንደማትቀበል አስታወቀች፤ ጥቂት ቆይታም ዘመዶቹ በአገሯ ባንኮች ያከማቹትን ገንዘብ ከመንቀሳቀስ ማገዷን ገለጸች።

መቸም መለስ ዜናዊ እና አዜብ ይሄንን ሲሰሙ ከኢትዮጵያ ህዝብ እየዘረፉ በአውሮፓ ባንኮች ያከማቹትን ገንዘብ ወደ ሌላ አገራት የማዛወሩን ጉዳይ ሳይመክሩበት አይቀሩም። የኛውን ዘረኛ አምባገነን እና ሚስቱን ከሚያስጠብባቸው ጉዳይ ውስጥ ትልቁ ከስልጣን የተባረርን ለታ ማን ያስጠጋናል የሚለው ጉዳይ ነው። መለስ ዜናዊ እንደሆን ከአረቦቹ ጋር ጠላት ነው። ምእራባውያን እጁ ደም ያለበትን አምባገነን አያስጠጉም። ቻይና እንደሆነች ለንግዷ ስትል ቀጥሎ ከሚመጣው መንግስት ጋር ግንኙነት ትፈልጋለች። ሌሎች የአፍሪካ አገሮች እሱን ከማስጠጋት ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችለውን የፖለቲካ ጫና ለመጋፈጥ አይፈልጉም። መለስ ዜናዊ በፈጸማቸው የዘር ማጥፋት እና የጦር ወንጀሎች ምክንያት ኢትዮጵያውያን፣ ሶማሌዎች እና የሌሎችም አገር ዜጎች በአለም ወንጀለኛ ፍርድ ቤት ፊት ለፊት ሊያቆሙት አሰፍስፈው የሚጠብቁት ሰው ነው። "ምን ይውጠኝ ይሆን?" የሚለው ጥያቄ አእምሮውን ጠዋት ማታ ሳያስጠብበው አይቀርም። ለዚህም ነው በጨነቀው ቁጥር ትግራይን አስገንጥሎ አዲስ አገር የመፍጠሩን ጉዳይ ለጓዶቹ የሚያስታውሳቸው።

ከኑሮ ውድነት እና ከስራ አጥነት ጋር የተያያዙ የተቃውሞ ሰልፎች በአፍሪካ እና በመካከለኛው ምስራቅ አገራት በፍጥነት እየተንሰራፉ ነው። ህዝቡ በሙስና በተዘፈቁ እና ከህዝብ በዘረፉት ሃብት ኪሳቸውን በሞሉ አምባገናዊ መሪዎች መገዛቱ በቃኝ እያለ ነው። በበርካታ አገራት ህዝባዊ አመጽ ተቀስቅሷል፤ የአገዛዞቹ ቁንጮዎችም ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ገብተዋል። ብዙዎቹ በቱኒዚያ የደረሰው እንዳይደርስባቸው ከወዲሁ የችኮላ እርምጃዎች እየወሰዱ ነው፤ በአንዳንድ ምርቶች ላይም የዋጋ ተመን አድርገዋል። መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ለማድረግ እየሞከረ ያለውም ይኸው ነው።

ዘረኛውን አምባገነን እና የወንጀል እና የዘረፋ ጓዶቹን ፍርሃት ሰቅዞ ይዟቸዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ከነዚህ የሰሜን አፍሪካ አገራት እጅጉን በባሰ ሁኔታ በአገዛዙ ከፍተኛ ጥቃት እና ግፍ ሲፈጸምበት ቆይቷል። ታዲያ የኛው አምባገነን የስጋን ዋጋ ከ70 ብር ወደ 52 ዝቅ አድርጎ እና የራሱን ጥፋት በነጋዴዎች ላይ አላኮ ህዝብ የሚያታልል መስሎታል። እንደለመደው የውሸት ቃል አዥጎድጉዶ፤ ለሃያ አመታት እንዳልገዛ ሁሉ፤ እድገት የሚመጣው ከአምስት አመታት በኋላ ነው እያለ እና የሃሰት ተስፋ እየመገበ ጊዜ መግዛት የሚችል መስሎታል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ብዙ ጥያቄዎች አሉት። እነዚህ ጥያቄዎችም ቁጣውን እያፈሉት ነው።

አዎን፥ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ጥያቄዎች አሉት፦

ለመሆኑ፥ የአገራችን ችግር የሁላችንም ነው ከተባለ፣ ድሆቹ እኛ ብቻ የሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? ለምንድን ነው መለስና አዜብ በሃብት ላይ ሃብት እየጨመሩ ሲሄዱ፣ እኛ ግን እየደኸየን ያለነው?

ለምንድን ነው የባለስልጣናቱ ልጆች በአስር ሺህ ዶላሮች የልደት ስጦታ ሲሰጣቸው እኛ ግን በባዶ ሆድ የምናድረው?

ለምንድን ነው ለባለስልጣናቱ ልጆች እስከ ውጭ አገር ድረስ በዶላር እየተከፈለ ጠባቂ ሲመደብላቸው እኛ ሽሮ እና ዘይት መግዣ ገንዘብ የሌለን?

ለምንድን ነው? ይላል የኢትዮጵያ ህዝብ።

ህዝቡ እየጠየቀ ነው...

- ለመሆኑ እንዴት ነው የውጭ አገር የግብርና ኩባንያዎች ከለም መሬታችን ላይ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገቢ እያገኙ፤ እኛ ግን አገራችን የተደጋጋሚ ድርቅ ሰለባ ስለሆነች ረሃቡን ቻሉት የምንባለው?
- እንዴት ነው መለስ፣ አዜብ፣ ስብሃት እና ሳሞራ ከህዝብ የዘረፉትን ገንዘብ ወደ ውጭ አገር ባንኮች እያሸሹ፤ እኛ ተርበንም ቢሆን በእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ስም ለወጣው እቅድ ገንዘብ አዋጡ ተብለን የምንገደደው?
- እድገት ፈጠራቸው የምንባለው ችግሮች ባለስልጣናቱን ሳይሆን እኛን ብቻ የሚጎዱት ለምን ይሆን?
- እኛ ከስራዎቻችን እየተባረርን ከባለስልጣናቱ ዘር የወጡ ምርጦች ግን እየተቀጠሩ ያሉት እንዴት ነው?
- እኛ ስራ አጥተን ስንቸገር ለነሱ አዳዲስ ስራዎችን የሚፈጥረው ተአምራዊ የመንግስት ፖሊሲስ ከየት ፈልቆ ይሆን?
- ለመሆኑ እኛ የኤሌክትሪክ ሃይል አጥሮን ስንቸገር እነሱ ገለልተኛ ቴሌቪዥን እና ሬድዮኖችን የሚያፍኑበትን ሃይል የሚያገኙት ከየት ነው?

የህዝቡ ጥያቄ በዚህም አያቆምም...

- መሬት በህገወጥ መንገድ በመሸጥ እና በማስተላለፍ ተከሰው የትናንሽ ከተሞች አስተዳዳሪዎች ሲታሰሩ፤ ከተማ የሚያካክሉ መሬቶች በዚሁ አኳኋን ከየቦታው የነጠቀችው አዜብ በነጻ የምትመላለሰው ለምንድን ነው?
- በመቶዎች የሚቆጠሩ ነጋዴዎች ግብር ባለመክፈል ስም እየተከሰሱ እስር ቤት ሲገቡ፤ የወያኔ ባለስልጣናት ንብረት የሆነው ኤፈርት እና ባለስልጣናቱ ግብር የማይከፍሉት ወይም ባለመክፈላቸው ፍርድ ፊት የማይቀርቡት ለምንድን ነው?
- ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ዜጎች ትናንሽ ወንጀሎችን በመፈጸማቸው በየቀኑ እየታሰሩ፤ በሙቶዎች የሚቆጠሩ ንጹሃንን በጠራራ ጸሃይ ያስጨፈጨፉት ቤተ መንግስት ውስጥ የሚቀመጡት እንዴት ነው?
- ጥቂት ዘረኞች የአገሪቱን ገንዘብ እየመዘበሩ፣ እኛ ግብር የምንከፍለው ለምንድን ነው?
- በየአመቱ ከአገሪቱ በጀት ውስጥ የሚጠፋው በቢሊዮኖች የሚቆጠር ብር የት እየሄደ ነው?
- ከወርቅ ማእድኖቻችን እየተጠቀመ ያለው ማነው?
- ለባእዳን ነጋዴዎች መሬት በማከፋፈል እየተጠቀመ ያለው ማነው?
- እኛ እንዲህ እየደኸየን የወያኔ ባለስልጣናት ባለሃብቶች የሆኑት እንዴት ነው? ለመሆኑ ሃብታቸው ከየት መጣ?
- ዝርፊያቸውን ካከናወኑ በኋላ ሃብታቸውን የሚያስመዘግቡት፤ እንዲሁም ሃብታቸውን በማስመዝገባቸው ተከታትሎ የሚቀጣቸው ሰው ያለ ለማስመሰል የሚሞክሩት ማንን ለማታለል ነው?

አዎን፥ ህዝቡ ይጠይቃል...

- ለመሆኑ ዴሞክራሲ አለ እየተባለን፣ ስልጣን ላይ ያሉት ሰዎች ግን በኛ ያልተመረጡበት ምክንያት ምንድን ነው?
- ሃሳባችሁን በነጻነት ግለጹ እየተባለ፣ ያንኑ ስናደርግ ግን የምንታሰረው፣ የምንደበደበው፣ የምንሰደደው፤ ለምንድን ነው?
- ንጹሃን ለሰቆቃ የሚዳረጉት ለምንድን ነው?
- እኩልነት አለ እየተባለን ከአንድ ዘር የተውጣጡ ምርጦች የፖለቲካን ስልጣን እና የአገሪቱን ኢኮኖሚ እንዲቆጣጠሩ እየተደረገ ያለው ለምንድን ነው?

(ወደ ገጽ 5 ዞሯል)

## የቱኒዚያዊያኑ የበቃኝ ርምጃና . . .

(ከገጽ 4 የዞረ)

ለምንድን ነው፣ ለምንድን ነው፣ ለምንድን ነው?

የኢትዮጵያ ህዝብ፥ እነዚህን እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እየጠየቀ ነው። መለስ ዜናዊ ግን እውነቱን ሊናገር እና ሊመልሳቸው አይችልም። ችግሩ ውሸታምነቱ ብቻ ሳይሆን፤ እውነቱን መናገር የሚወነጅለው እራሱኑ መሆኑ ነው።

የመለስ ዜናዊ እና የቤን አሊ አገዛዞች ብዙ ተመሳሳይነት አላቸው...ሁለቱም ዴሞክራሲን በማስፈን እና ለውጥን በማምጣት ስም ስልጣን ያዙ፤ ነገር ግን አፈናን፣ ፍርሃትን፣ ዘረፋን፣ ሙስናን፣ አድሎን፣ የኑሮ ውድነት ለየህዝቦቻቸው ሰጡ። ሁለቱም ይዋሻሉ፤ ላልተወሰነ ጊዜ ስልጣን ጨብጠው ለመቆየት ይሻሉ።

ቤን አሊ የመንግስትን ስልጣን ተገን በማድረግ ለመጣበት ነገድ አባላት እና ለቤተሰብ ዘመዶቹ ሃብት አጋበሰ። መለስ ዜናዊም በዘር ለተሳሰሩት ምርጦች ኢኮኖሚውን እና የፖለቲካን ስልጣን ሰጥቷል። የቤን አሊ ሚስት ላይላ ትራቤልሲ ከህዝብ በሰረቀችው ገንዘብ ሃብታም ሆነች፤ አዜብ መስፍንም እንዲሁ። ላይላ ትራቤልሲ ዘራፊነቷን ለመደበቅ እራሷን እንደ በጎ አድራጊ ለመቅረጽ ትሞክራለች፤ አዜብ መስፍንም እንዲሁ።

ይህ ሁሉ ሃብት ማግበስበስ፤ ይህ ሁሉ በዘር መደራጀት ግን ህዝብ ተቆጥቶ የተነሳ ለታ አያድናቸውም። ምእራባውያን አገራትም መንገዳገዳቸውን ሲያዩ ጥለዋቸው ይሮጣሉ።

ብዙዎች ስለ ቱኒዚያ የወደፊት ሁኔታ ከወዲሁ ጥያቄ እያነሱ ነው። የጀመሩት ለውጥ ከዳር ይደርስላቸው ይሆን? ሌላ አምባገነን ይነግስባቸው ይሆን? ወደ እርስ በእርስ ጦርነት ያመሩ ይሆን? እና የመሳሰሉት...

ማን ያውቃል? የቱኒዚያ ህዝብ በዚህ ሁሉ ፈተና ውስጥ ያልፍ ይሆናል። ነገር ግን ቢሳሳት እንኳ፤ እንደማንኛውም ህዝብ ከስህተቱ ሊማር ይችላል። ዴሞክራሲ ማለት ህዝብ ፈጽሞ የማይሳሳትበት ስርአት ማለት አይደለም። ዴሞክራሲ ማለት ህዝብ በፈቃዱ የሚገዛበት እና ስህተት ሲፈጽምም፤ ከስህተቱ የሚማርበት፤ በራሱ ፍጥነት የሚጓዝበት እና የሚያድግበት ስርአት ማለት ነው። "በእኔ አውቅላችኋለሁ" መርህ የሚገዙን አምባገነኖች የሚቀሙንም ይህን ተፈጥሯዊ መብት ነው፤ ከራሳችን ስህተት የመማር መብት!

ያም ሆነ ይህ፤ የቱኒዚያ ህዝብ ድምጹን አሰምቷል! ምን እንደሚፈልግ ተናግሯል! ጉልበቱንም አሳይቷል! ይህ፥ ወደፊት ለሚመጡትም ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ነው።

መለስ ዜናዊ ህዝብ በቁጣ መነሳቱ የጊዜ ጉዳይ ሆኖ እንጂ የማይቀር እንደሆነ ያውቃል። ለዛች ቀንም ሁልጊዜም ቢሆን ይዘጋጃል። ታስረው እንደሰለጠኑ ውሾች ለሱ ብቻ የሚታዘዙ ወታደሮችን ከማሰልጠን አንስቶ፤ በዘር እየከፋፈለ ህዝብ በማጋጨት አይኖችን ከራሱ ላይ የማስነሳት ስራውን በየአቅጣጫው ተሰራጭተው የሚሰሩለትን ቅጥረኞች በማስቀመት ሁሌም እንደተዘጋጀ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ህዝቡን በሃይማኖት መከፋፈልን እንደ ጭንቅ ቀን መውጫው በመቁጠር የመሰረት ስራ ሲሰራ ቆይቷል።

አዎን፥ የተጠበቡ አምባገነኖች፣ እነሱ ሲሄዱ ሰላም እንዳይኖር ለማድረግ እና ህዝቡ እነሱን በማስወገዱ እንዲጸጸት ብዙ ተንኮል ይሸርባሉ። ይሁን እንጂ፥ ደግመው ደጋግመው እንዳፈሩ የአለማችን ታሪክ አሳይቷል።

መለስ ዜናዊ ከስልጣን ይባረራል። ኢትዮጵያም እንደሱ ምኞት ወደ እርስ በርስ ግጭት እና ደም መፋሰስ አትገባም! ለዘላለም ትኖራለች፤ ድንበሯ ይሰፋል፤ ታብባለች፤ ልጆቿም በሰላም ይኖራሉ!

ለዘረኛው አምባገነን ምእራባውያን ደጋፊዎች አንድ መልክት አለን። አንድ የመካከለኛው ምስራቅ አገር ጸሃፊ ከጻፉት ጽሁፍ የተወሰደ ቅንጫቢ እነሆ፦

"'ጠብቀን የሚሆነውን እንይ' የሚለው የዩናይትድ ስቴትስ አካሄድ ከዚህ በኋላ በቂ አይደለም።...አሁን ህዝቡ ካሸነፈ በኋላ መደገፉ ቀላል ነው። ኦባማ ስልጣን ላይ በቆዩባቸው ሁለት አመታት፣ እሳቸውም ሆኑ የአስተዳደራቸው ባለስልጣናት፣ የቱኒዚያን ህዝብ መሰረታዊ መብት ደግፈው ቆመው አላየንም። ለኦባማ አስተዳደር፣ እውነተኛው ፈተና ያለው አሁን ነው፤ ህዝቡ እርዳታቸውን በሚፈልገበት ወቅት።"

የኛም መልክት ይኸው ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ የሚፈልገው በራሱ ጉልበት ካሸነፈ በኋላ "እንኳን ደስ ያለህ" እያሉ የሚመጡትን አይደለም። በመከራው ጊዜ ከጎኑ የሚቆሙትን ነው።

ይሁን እንጂ፤ እነሱ ረዱም አልረዱም፤ ነፍሰ ገዳዩን አገዛዝ መደገፋቸውን አቆሙም አላቆሙም፤ መለስን የቤን አሊ እና ከሱ ቀድመው በህዝብ አመጽ ከስልጣን የተባረሩ ብዙ አምባገነኖች እጣ እንደሚገጥመው ጥርጥር የለውም!

**የኢትዮጵያ ህዝብ ድል ያደርጋል!**

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መዋቅራዊ . . .

(ከገጽ 2 የዞረ)

በአየር መንገዱ ውስጥ የሚሰሩ ምንጮች ለሪፖርተራችን እንደገለጹት፥ ድርጅቱ ቀስ በቀስ የአንድ ቤተሰብ ንብረት እየመሰለ ሄዷል። ከቁልፍ ባለስልጣናቱ ጀምሮ እስከ በረራ አስተናጋጆች ድረስ ሆን ተብሎ የገገርው ቡድን አባላት እንዲሆኑ እየተደረገ ነው ብለዋል።

## የትግራዩ ገዢ ቡድን በርካታ ንግድ ቤቶችን ዘጋ፤ ህዝቡ "ይህ ለኛ አይደለም" እያለ ነው

ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ በገዛ እጁ ለፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ ነጋዴዎችን ተጠያቂ ለማድረግ እና ኢኮኖሚውን ከአንድ ዘር በተውጣጡ ምርጦች ቁጥጥር ስር ለማኖር የሚያደርገውን ሩጫ እንደገፋበት ከሰሞኑ የወጡ ዘገባዎች ገለጹ።

ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በአዲስ አበባ ብቻ በአስርት የሚቆጠሩ ንግድ ቤቶች መዘጋታቸውን ሪፖርተራችን ገልጿል። ሬውተርስ የዜና አገልግሎት በበኩሉ እስከ ሐሙስ ድረስ 103 የችርቻሮ ንግድ ቤቶች እንደተዘጉ ዘግቧል። ነጋዴዎቹ የተቀጡት ባለፈው ሳምንት የተዋወቀውን የዋጋ ማስተካከያ በስራ ላይ አላዋላችሁም በሚል ነው።

ንግድ ቤቶችን የመዝጋቱ ዘመቻ እንደሚቀጥል እና አዋጁን በስራ ላይ አውለው ያልተገኙ ነጋዴዎችም የገንዘብ እና የእስር ቅጣት እንደሚደረግባቸው ለማወቅ ተችሏል።

አዲሱ አዋጅ የጅምላ ነጋዴዎችን እንጂ እነሱን እንደማይመለከት ተነግሯቸው የነበሩት ቸርቻሪዎች፤ የዋጋ ማስተካከያው ከተላለፈ በኋላ ሌላው ቀርቶ የሂሳብ ማወራረጃ ማሽናቸውን ወይም "ካሽ ሬጂስተሮችን" እንዲያስተካክሉ ጊዜ አልተሰጣቸውም። በሱቆቻቸው የሞሏቸውን እቃዎች ከጅምላ ነጋዴዎች የገዙት በቀድሞው ዋጋ በመሆኑም በርካቶች ከፍተኛ ኪሳራን እንደሚቀምሱ ይጠበቃል። የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች የአገሪቱ የዋጋ ንረት እየጨመረ እንደሚሄድ ቀድሞውኑ ሲተነብዩ የቆዩ ሲሆን፤ አገዛዙ ያወጣው የዋጋ ገደብ ህገ-ወጥ ንግድ እንዲስፋፋ በማድረግ ቁሳቁሶችን የባሰ እንደሚያስወድድ ይናገራሉ።

የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ያናገራቸው ነዋሪዎች አገዛዙ የወሰደው እርምጃ ህዝብ እንዲጠቅም የታለመ አይደለም ይላሉ። በመለስ ዜናዊ እርምጃዎች ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ እንዳላቸው የተናገሩት አንድ ግለሰብ፣ አዲሱ አዋጅ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ብቻ የተላለፈ እንደሆነና እነሱ ለፈጠሩት ችግር ህዝቡ ነጋዴዎችን እንዲወቅስ ለማድረግ ነው ብለዋል። የዋጋ ገደቡ ለተወሰነ ጊዜ ይረጋ እንደሆን እንጂ በዘላቂነት ሊቀጥል ይችላል ብለው እንደማያምኑም ለዘጋቢያችን ነግረዋል።

## የጂቡቲ መንግስት የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ከወያኔ በማግኘቱ ላይ እምነት የለውም ተባለ

የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ከኢትዮጵያ ለመግዛት በወያኔ ቁጥጥር ስር ካለው የኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን ጋር ኮንትራት ተፈራርማ የነበረችው ጅቡቲ በአገዛዙ ብቃት ላይ እምነት እንደሌላት ከአሜሪካ ኤምባሲ የወጣ የሚስጥር መልክት አጋልጧል።

ዊኪሊክስ በተባለው ድረ-ገጽ ላይ የወጣው እና በጅቡቲ ካለው የአሜሪካ ኤምባሲ የተላከው መልክት፤ ጂቡቲ ከወያኔ አገዛዝ ጋር የተፈራረመችው ውል ላለባት የሃይል ቀውስ መፍትሄ ይሆነኛል ብላ ተስፋ አድርጋ ቢሆንም፤ ወያኔ በገዛ አገሩ እያሳየ ያለው የብቃት ጉድለት ለአገሪቱ ተስፋ አስቆራጭ ሆኗል። የጂቡቲ የኢነርጂ ሚኒስቴር ለአሜሪካው አምባሳደር እንደነገሩት፥ በኢትዮጵያ ከኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ጋር የተያያዙ ግንባታዎች መዘግየት እና በድርቅ የሚሳበበው የሃይል እጥረት አገራቸውን ለስጋት ዳርጓል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፥ በወያኔ ቁጥጥር ስር ያለው የኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን ገና አቅርቦቱ ሳይሳካለት ከጅቡቲ እና ከሱዳን ጋር በተዋዋለው ውል ላይ የዋጋ ጭማሬ ለማድረግ እንቅስቃሴ ላይ እንዳለ ታውቋል። ምንም እንኳ ባለስልጣናቱ ገንዘብ ከአገር ማሸሻቸውን ቢቀጥሉም፤ አገዛዙ ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት ቀውስ እንዳለበት ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን በከፍተኛ የብቃት ጉድለት የሚተዳደር ድርጅት ሲሆን፤ አሰራሩን ለማሻሻል ባለመቻሉም መፍትሄ ይሆናል በሚል ሶስት ቦታ ለመከፋፈል በዝግጅት ላይ እንዳለ ካፒታል የተባለው የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ዘግቧል። አንድ የፖለቲካ ተንታኝ፥ "ይህ ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም" የሚባለው አይነት ነው ፤ መሰረታዊው ችግር ሳይቀረፍ የመዋቅር ለውጥ ምንም መፍትሄ አያመጣም ብለዋል። የአገሪቱ የተማረ የሰው ሃይል ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ቁጥር መሰደዱን እስከቀጠለ ድረስ፣ በሁሉም የመንግስት ተቋማት ውስጥ የሚታየው የብቃት ጉድለት እና አስተዳደራዊ በደል እየከፋ እንጂ እየተሻሻለ አይሄድም ሲሉ አስረድተዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org